# ለኢትዮጵያ ተማሪዎች በሙሉ /ዓለም አቀፍ የኢ/ያ ተማሪዎች ሕብረት ስለማቓቓም/

አገራችን ኢ/ያ ከጥንት ጀምራ ከአገራቸዉ አልፎው በዓለማችን የትላልቅ የፈጠራ ስራዎች ባለቤት የሆኑ ሙሁራን መፍለቂያ መሆንዋ ያለፈዉና አሁንም ያለው ነባራዊ ሁኔታ የሚመሰክረዉ እዉነት ነው። ይሁን እንጂ እንደ ዕድል ሆኖ አገራችን ኢ/ያ ልክ እንደ የአባይ ዉሃ የተማሩ ልጆችዋን ልትጠቀምባቸዉ አልታደለችም። አባይ የአገራችን አፈር እየጠራረገ በሺዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ተጉዞ ለባእድ አገሮች የቅርብ ዘመድ ሆኖ ያገለግላል። በተማሳሳይ መልኩ እናት አገራችን ለነጌ ይሆኑኛል : ከረሃብና ከድንቁርና ያላቅቁኛል እያለች የምታስተምራቸዉ ሙሁራንም የሌላ አገር ሃብት ሲሆኑ ቆይቶዋል አሁንም በተግባር የምናየዉ ይህ እዉነት ነው።

አገራችን ድሃ አይደለችም ብናምንም ባናምንም አገራችን በጣም ሃብታም አገር ናት። ይሁን እንጂ እኛ ልጆችዋ በተለይም ተምረናል የምንል : ምሳሌ ሁነን መገኘት የሚጠበቅብን : ሌላ ወገናችን እንመራለን ተብለን የሚታመንብን የህብረተሰባችን ዜጎች ግን የአስተሳሰብና የመቻቻል ድህነት አለብን ብንል የተጋነነ አይሆንም። እዉነት ነዉ አገራችን የብዙ ብሄር ብሄረ ሰዎች ስብስብ ናት ይህ ደግሞ **የምንኮራበትና የምንመካበት ዉበታችን** ነው። ይህ እግዚአብሄር የሰጠን ዉበታችን ጠብቀን አገራችን ጠንካራና የማትደፈር **የአፍሪካ መዲና** ለማድረግ በአንድ የአገር ፍቅር ጥላ ታቅፈን መስራትና ትናንት በአያቶታችን ደም ያገኘናት አገር በተሻለ መልኩ ለሚቀጥለዉ ትዉልድ ማስተላለፍ ይጠበቅብናል።

የዚህ ጥሪ ዋነኛዉ ዓላማ በኛ የለዉጥ ሃይሎች እንዲሁም የነጌ አገር ተረካቢዎች ተብለን የሚነገርለን በወጣትነት ዕድሜ ላለን ተማሪዎች ይመለከታል።ከታሪክ እንደተማርነዉ የአገራችን ተማሪዎች በአገራችን ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ የለዉጥ ሃይሎች ሲሆኑ ቆይቶዋል። ካሁኑ በፊት በነበሩ ስርዓቶች ተማሪው የሰላም መልእክተኛ በመሆን ህዝባችን ከነበሩ ጨቓኝ ስርዓቶች ግንባር ለግንባር በመወጋት አሁን ላለንበት የሰላም ግዜ አድርሶናል።

**የሚቀጥለዉ ጥያቄ ከኛ ከዚህ ትውልድ ወጣት ተማሪዎች ምን ይጠበቃል? የሚል ይሆናል።**

ሁላችን የማንክደዉ ሁላችን ሊያስማማ የሚችል አንድ ነገር አለ። እሱም በአገራችን ሰላም ተፈጥሮዋል። ራሳችን ህብረት ፈጥረን የራሳችን መብት የምናስከብርበት: መብታችን የምንጠይቅበት: ለአገራችን ባለን አቅምና ችሎታ የምናገለግልበት: ሳይማር ላስተማረን የአገራችን ገበሬ አለንልህ የምንልበት መብት በእጃችን አገኛል።

ይሁን እንጂ የአሁኑ የአገራችን ወጣት ሙሁር/ተማሪዎች/ በሁለት ጎራ የተከፈለ ይመስላል። አንደኛዉ የምን አገባኝ ስሜት ይዞ በርቀት የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ንፋሱ ወደ ሚነፍሰዉ በራሱ አስተሳሰብ ሳይሆን በሰዎች አስተሳሰብ የሚገራ ወጣት ሙሁር ነው። ሁለቱ ጎራዎች ከተማረ የአንድ አገር ዜጋ የሚጠበቁ አይደሉም። የተማረ ወጣት የለዉጥ ሃወርያት ሊሆን ይገባል። ይህ ሲባል ደግሞ አርቆ አሳቢ: በራሱ የሚተማመን: ሃላፊነት መሸከም የሚችል ወ.ዘ.ተ መሆን ይኖርበታል።

የተከበራቹ የአገራችን ተማሪዎች ሁላችን የተለያየ የፖለቲካ አስተሳሰብ: እምነት:የሂዎት መሪህ ወ.ዘ.ተ ይኖረናል ይሁን እንጂ በአገራችን ጉዳይ ግን አንድ እና አንድ ብቻ መሆን ይጠበቅብናል። የዚህ ጥሪ ዓላማም ሁላችን ወጣት ሙሁራንና ተማሪዎች ከሁሉ በፊት ለአገራችን ቅድምያ በመስጠት በትምህርት ዙርያ መሰረታዊ ለዉጥ የሚያመጣ የጋራና የተደራጀ በአንድ ዓለማቀፍ የኢ/ያ ተማሪዎች ህብረት ጥላ ሁነን እንድንሰራ ለመወያየትና ከዛ አልፎም ህብረቱን በቅርብ ግዜ ተቃቁሞ ስራው የሚጀምርበት ሁኔታ ለማመቻቸት ነው።

**ለመሆኑ እኛ ወጣት ተማሪዎች ምን ምን ማድረግ እንችላለን?**

እኛ ወጣት ተማሪዎች ለአገራችን በብዙ መልክ ማገልገልና ወገናችንም መርዳት እንችላለን። በአሁኑ ግዜ በአገረችን የኛ የወጣት ተማሪዎችና ሙሁራን ተሳትፎ የሚሹ ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህ መካከለም:

1. ለእናት አገራችን በተማርነዉ የትምህርት መስክ እና በሌሎች ተማሳሳይ ነገሮች ብዙ መስራት እንችላለን

2. በዉጭ አገር ያገኘነዉ ልምድ እና ተሞክሮ በእናት አገራችን ተግባራዊ መድረግ

3. በአገራችን ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች የሚጠናከሩበትና ተማሪዎችም ለትምህርታቸዉ የሚነሳሱበት ስራዎች ማካሄድ

4. በአገራችን አንድ ደረጃዉ የጠበቀ **ማእከላዊ የምርምር ላቦራቶሪ** (National Central Laboratory or National Research Institute) እንዲቓቓም ማድረግ እና በተለያዩ በዉጭ አገር የሚገኙ የአገራችን ሙሁራን ለአገራቸዉ የሚረዱበት ሁኔታዎች ማመቻቸት

5. በተለያዩ ምክንያቶች በዉጭ አገር የሚኖሩ የአገራችን ሙሁራን እና ሌሎች ዜጎች ከመንግስታችን ጋር ማግባባትና ለእናት አገራቸዉ ያካበቱት ልምድና ትምህርት እንዲያካፍሉ ሁኔታዎች ማመቻቸት

6. የአገራችን ተማሪዎች በሳይነስና ቴክኖሎጂ ዙርያ የሚወያዩበትና የፈጠራ ችሎታቸዉ የሚያሳድጉበት መድረክ መፍጠር

7. በአገራችን ከታች ከአንደኛ ደረጃ ት/ቤት እስከ የከፍተኛ ት/ት ተቓማት ያሉ ቤተ ሙኮራዎች (Laboratoires) በቁሳቁስና በሰው ሃይል ማደራጀት

8. ተማሪዎቻችን ከታች ጀምሮው በቤተ ፈተነ የተደገፈ ት/ት እንዲያገኙና የምርምር ክህሎችን አብሮቸዉ እንዲያድግ ማድረግ

9. መንግስት በዉጭ አገር ተምረዉ ወደ እናት አገራቸዉ የሚመለሱ ተማሪዎች የሚያበራታትበትና ሁኔታዎች ማመቻቸት

10. በአገራችን በሚፈጠሩ የፖለቲካ እና ሌላ ተማሳሳይ ችግሮች ወጣት ተማሪዉ መንጎኛ በመሆን በመንግስትና በተቓሚዎች እርቅ እንዲኖር የበኩላችን ማበርከት

11. ሌሎች ወ.ዘ.ተ

በአጠቃላሊ የህብረቱ የመጀመሪያዉና ዋነኛዉ ዓላማ **ዓለም አቀፍ የኢ/ያ የተማሪዎች ህብረት** በማቓቓም በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችና ሙሁራን በጋራ ትምህርት ነክና በመሳሰሉ ጉዳዮች ለእናት አገራችንና ሳይማር ላስተማረን የአገራችን ህዝብ ዜግኔታዉ ግዴታ እንድንወጣ የሚያስችለን መድረክ መፍጠር ነዉ::

እነዚህ ልንሰራቸዉ ከምንችላቸዉ ብዙ ነገሮች ጥቂቶቹ ናቸዉ:: እያንዳንዱ የአገራችን ሰዉ እኛ እንድንማር በኛ ገንዘቡ: ጉልበቱ ወ.ዘ.ተ አፍሥሶዋል:: እኛ ደግሞ ለእናት አግራችንና ወርቅ ለሆነ ህዝባችን ዉሌታ ከፋዮች ሁነን መገኘት ይኖርብናል::መንግስታችን እንዲሁም ሁሉ አገር ወዳጅ ኢትዮጵያዊ ወገናችን ከኛ ጎን እንደሚሆንም ጥርጥር የለንም::

ዉድ የአገራችን ተማሪዎች እነዚህና ሌሎች ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የኛ የወጣት ተማሪዎች በጋራ መስራት: መናበብና መደማመጥ የግድ ይለናል::ይህ እዉን የሚሆነው ደግሞ እኛ እርስበርሳችን : ከመንግስታችንና ከሌሎች የሚመለከታቸዉ ኢትዮጵያዉያን የምንገናኝበት በጋራ ድምጻችን የምናሰማበት መድረክ እንዲኖረን የግድ ይላል:: እስከ ዛሬ ሁላችን በግልም ይሁን በቡድን ስንመካከር ቆይቶናል:: በመጨረሻም የተወሰን ተማሪዎች ለምን ዓለም አቅፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ህብረት አይኖረንም ብለን በመወያየትና በአውሮፓም በተለይም በፈረንሳይ (ፓሪስ) እና በጀርመን ከሚኖሩ አገር ወዳጅ ኢ/ያዉያን በመወያየት ይህ ጥሪ ለማስተጋባት ዉሳኔ ላይ ደርሰናል:: ስለዚህ ዉድ የአገራችን ተማሪዎች: ሙሁራንና ሌሎች ወገኖችን የሚኖራቹህ አስተያየት: ምክር እንዲሁም ምስረታዉ እዉን ለማድርግ በምናደርገዉ ዝግጅት ዋነኛዉ ተሳታፊዎች እንድትሆኑ በአክብሮት እንጠይቃለን::

**እጅ ለእጅ ተያይዘን ሳይማር ላስተማረን ወገናችን ለመርዳት ዛሬ በአንድነት እንነሳ::**

Adhock Committee members of the Worldwide Union of Ethiopian Students

France, Paris

Union_ethiostudents@yahoo.com